የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ሶስተኛ ዓመት ቁጥር 5ኛ
ሠመራ ሚያዝያ 4 ቀን 1998 ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th year No. 33
SEMERA- 12th,Aprile 2005

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት

አዋጅ ..... ገጽ ፪

አዋጅ ቁጥር 5/1991

የአፋር ብሄራዊ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንት አዋጅ፣

የአፋርን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠንና የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል ኢንቨስትመንትን ማበረታትና ማስፋፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የክልሉን ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማጠናከር የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ተሳትፎ ማስፋፋትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

የክልሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የሚመራበት ስርዓትን ማስያዝ በማስፈለጉ፣

እንዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፕብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ ቁጥር ፴፱ ንዑስ ቁጥር ፭፫/፫ ለክልል መንግስት ህገ መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. <u>አጭር ርዕስ፡</u>

ይህ አዋጅ «የአፋር ብሄራዊ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንት አዋጅ ፱/፪፻፲ »ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ትርጉም</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡

፩.«ኢንቨስትመንት»ማለት አዲስ ድርጅት ለመቋቋም ወይም ነባር ድርጅት ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል ባለሀብት የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው።

፪. «ድርጅት» ማለት ለትርፍ ሲባል የተቋቋመ ድርጅት ነው።

፫.«ካፒታል» ማለት የሚተላለፍ ሰነድ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ ህንፃ ማደሻ የስራ ማስኬጃ መብት የፓተንት መብት ወይም ሌላ የንግድ ሀብት ነው።

፬.ሰው ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፭. ባለሃብት ማለት በክልሉ ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪፻፭ ቁጥሮች ችና ፭/፬ እና ፭/፮ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል።

፮. ክልል ማለት የአፋር ብሄራዊ ክልል መንግስት ነው።

፯. ጽህፈት ቤት ማለት የኢንቨስትመንት ጽህፈት ቤት ነው።

፰. ቦርድ ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ የተመለከተው አካል ነው።

፱. ኮሚቴ ማለት የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መ/ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነው። እንደደ አስፈላጊነቱ የዞን ፣የወረዳ ኮሚቴ ነው።

፲.የሚመለከተው አካል ማለት በዚህ ዋጅ ውስጥ ስለተጠቃለለት ጉዳዩች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኃላፊነት የሚመለከተው የማዕከላዊ መንግስት ወይም የክልል መንግስት ወይም የክልል በህግ ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል ነው።

፫. <u>የኢንቨስትመንት አካል መቋቋም፡</u>

በአፋር ብሄራዊ ክልላ መንግስት ም/ቤት የኢንቨስትመንት አካላት /ከዚህ በኃላ የኢንቨስትመንት አካላት/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፬. <u>ዓላማ፡</u>

በኢንቨስትመንት አዋጅ በአንቀጽ(፬) ከተመለከተው ሌላ የኢንቨስትመንት አካላት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል

ሀ) የክልሉን ማህበራዊ አገልግሎት ማጎልበትና ዕድገቱን ማበረታታት።

ለ) የክልሉን ሕብረተሰብ በምግብ እራሱን እንዲችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አስፈላጊ ሁኔታዎች ማመቻቸት ማጠናከር፡

ሐ. የክልሉን ሕብረተሰብ በተለይም ግብርና ኢንዱስትሪ እንዲሁም የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ማበረታታት።

መ) የክልሉን ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋልና ለልማት ኢንቨስተሮችን ማበረታታት፡

ሠ) የክልሉን የገቢ ምንጭ ማሳደግ፡

ረ) ወደ ውጭየሚላኩ የክልሉ ምርቶች በመጠን የጥራትና በዓይነት እንዲያድግ ማበረታታት ፡

ሰ) የክልሉ ህብረተሰብ የስራ ዕድል መከፈት፡

፭. <u>ቦርድ</u>

ቦርድ ተጠሪነቱ ለኮሚቴውና ለክልሉ ሬዝደንት ሲሆን እንደሚከተለው ተቋቁሟል።

ለ) የአፋር ብ/ክ መንግስት የኢኮ/መ/ኃላፊ አባል

ሐ) ›› ›› ›› የፕላንና ኢኮ//ዘ/ ኃላፊ አባል

መ) ›› ›› ›› የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ አባል

ሠ) ›› ›› ›› የግብርና ቢሮ ኃላፊ አባል

ረ) ›› ›› ›› የሴቶቸጉዳይ ቢሮ.....››

ሰ) ›› ›› ›› ንግድ/ኢንዱ/ትራ /ቱሪ ቢሮ ኃላፊ.››

ሸ) ›› ›› ›› የሥራና ከ/ል/ማዕ/ኢ/ .....አባል

ቀ) ›› ›› ›› የውሃብት ልማት /ቢሮ .....አባል

በ) ›› ›› ›› የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ

፮. <u>የቦርድ ስብሳቢዎች</u>

፩.ቦርድ በወር አንደ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደርግ ይችላል፤፤

፪.ከቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በቦርድ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፤፤

፫.የቦርድ ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንድሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤፤

፬.የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱ የስብሰባ ሥነ ስርዓት ደንብ ያወጣል፤፤

፯. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

፩. የዚህን አዋጅ አፈፃፀምና የኢንቨስትንት ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፣ይመራል ፤፤

፪.በኢንቨስትመንት ፖሊሲው ላይ ለሚነሱ ጉዳዮች ውሳኔ ይሰጣል፤፤

፫.ይህንን አዋጅ መሠረት ያደረገ ደንብ ለማውጣትና ለማስፈፅም የሚስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል ፤፤

፬.በኢንቨስትመንት ፈቃድና ከማበረታቻዎች አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በሚቀርቡት የይግባኝ አቤቱታ ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤፤

፭.ጽህፈት ቤቱ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚስከፍለውን ክፍያ ይወስናል፣

፮.የጽህፈት ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅርና ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመሪያ ያፀድቃል፣

፯ .የሚያወጣውን መመሪያ ኢንቨስተሮች በግልፅ እንዲውቁት ያደርጋል፤፤

፰.የክልሉን ኢንቨስትመንት ለማረታታት አስፈላጊ መመሪያዎች ያወጣል፤፤

፱.የዞን የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ያደራጃል ይቆጣጠራል ይከታተላል፤፤

፲. የአዋጁን አፈፃፀም ና ተጓዳኝ ጉዳዮችን ይወስናል ተግባራዊነታቸውንም ያረጋግጣል፤፤

፲፩.ይህንን አዋጅና ሌሎችን መሠረት በማድረግ በቦርድ የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በኮሚቴው ሲፀድቁ ብቻ ይሆናል፤፤

፲፪.የኢንቨስትመንት ፅህፈት ቤትን ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ይጠቀማል፤፤

፰. <u>የኢንቨስትመንት ፅህፈት ቤት፤</u>

፩. የኢንቨስትመንት ፅህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለኮሚቴውና ለአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ም/ቤት ፕሬዚዳንት ይሆናል፤፤

፪.የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡

፫. <u>.የኢንቨስትመንት ፅህፈትቤት ሥልጣንና ተግባር፤</u>

፰.የክልሉን የኢንቨስትመንት ጉዳዮች ይመራል እንቅስቃሴውንም ያብረታታል ያስተባብራል ያስፋፋል፤፤

፱. ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሊወስዱ የሚገቡ የፖሊስና የአፈፃፀም እርምጃዎችን ያመነጫል ለቦርድ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፲. የክልሉን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አዲስ መረጃዎችን ይሰበስባል ያገናኛል ያሰራጫል ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ያስተዋውቃል በግብርና በኢንዱስት በኮንስትራክሽን በመንገድ ትራንስፖርት፤

፲፩. የክልሉን ኢንቨስትምንት ለማበረታታት ይህንን አዋ ጅ ተደግፎ ለአፈፃጸሙ ደንብና መመሪያ ያዘጋጃል ። የኢ/ፊ/ዲ/ሪ/መ የኢንቨስትመንት ባለስልጣን ደንብና መሪያዎችን ያስፈፅማል።

፲፪.ኢንቨስትምንትን ለማበረታታት ሚጠቅሙ ኤግዚቢሽኖችን ስብስባዎች፤ ስልጠናዎች ሴሚናሮች የመሳሰሉትን እንደ አግባቡ በክልሉ ያካሂዳል ለባለሃብቶች የምክር ድጋፍ ይሰጣል፣

፲፫.ኢንቪስትመንት ለማስፋፋት በባለሃብቶችና በመንግስታዊ መ/ቤቶች በመስተዳድሮችና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው መካከል ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤፤

፲፬.ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚረዱ ፁሁፎችን መግለጫዎችን ፊልሞችንና የመሳሰሉትን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፤፤

፲፭.ከባለሃብቶች የሚቀርቡ ፕሮጀክቶችን፣ የፕሮጀክት ፋይሎችን መርምሮ በማጥናት ለክልሉ ልማት ይጠቅማል ለሚለው የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተጠየቀው በ 15 ቀናት ውስጥ ይሰጣል፣ የማበረታቻ ጥያቄዎች ላይ ይወስናል፤፤

፲፮.የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሃብቶች ኢንቨስትመንት ፈቃድ የያዛቸውን ግዴታዎችና ሁኔታዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ፈቃዶችንም መዝግቦ ይይዛል፤፤

፲፯.በዞን በወረዳ ሪፖርቶቱን ይሰበስባል፣ ለቦርድ ያቀርባል፤፤

፲፰.የጽህፈት ቤቱን ንብረት በጥንቃቄ ይይዛል፤

፲፱.በኢንቨስትመንት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ ከነመፍትሔ ሃሳብም ለቦርድ ያቀርባል።

፳.ሌሎች ከበላይ አካል የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤

፳፩.በሕጉ ለክልሉና ለኅብረተሰብ ጠቃሚ ያልሆኑትን የኢንቨስትመንት ማመልከቻ ጥያቄም ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲. <u>የፅፈት ቤቱ ኃላፊዎች ሹመትና ተጠሪነት፤</u>

፩.የጽፈት ቤቱ ኃላፊ በክልሉ መንግሥት ም/ቤት ፕሬዚዳንት አቅራቢነት ይሾማሉ፤

፪.የጽህፈት ቤቱን የስራ ፕሮግራም በጀት አዘጋጅቶ ለክልል ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፈቀደም በስራ ላይ ያውላል።

፫. ለጽህፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል በህጉ መሰረት ተፈላጊ የሆኑት ሠራተኞች እንዲቀጠሩ ያደርጋል፣

፬. የጽ/ቤቱን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባሉ።

፲፭. የገቢ ምንጭ፤

ጽህፈት ቤቱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፣

ሸ. ክልል ም/ቤት በበጀት መደብ የሚሰጠው ገንዘብ ፤

ቀ. ከሚሰበሰበው የአገልግሎት ክፍያ

በ. ከማናቻም ሌላ ምንጭ የሚገኝ ገቢ ዕርዳታና ስጦታ፤

፲፮. <u>የሂሳብ መዛግብት፤</u>

ሸ የጽ/ቤቱ ተገቢ የሆነ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶችን ይጠብቃል።

ቀ. የጽ/ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶችና ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በክልል ኦዲት ጽ/ቤት ይመረመራሉ።

፲፫. <u>መሬት ስለማግኘት፤</u>

ሸ. ለተፈቀደ ኢንቨስትመንት የመሬት ጥያቄ የቀረበለት የክልል ቦርዱ የፌደራሉና የክልል ህግ መሰረት በማድረግ ጥያቄው በቀረበለት በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠየቀውን መሬት በኢንቨስትምንት ጽ/ቤት አካላት በኩል ለባለሀብቱ ያስረክባል።

ቀ. የዞንና የወረዳ መስተዳድሮች ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል መሬት በመመደብና የመደቧቸውን መሬቶች የሚመለከት መረጃዎችን ለኢንቨስትመንት አካላት ያሰተላልፋሉ።

በ. የክልሉ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ለተፈቀደው ፕሮጀክቶች መሬት ይሰጣል።

፲፬. <u>የኢንቨስትመንት ኮሚቴ ማቋቋም፤</u>

ሸ.የኢንቨስትመንት ኮሚቴ በዞንና በወረዳ ደረጃ ይቋቋማል፤

ቀ. የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሲሆን የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ይሆናል፣

በ. የዞን መስተዳድር ወይም ም/ቤት ለኢንቨስትመንት ኮሚቴ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

፲፯. <u>የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ አባላት፤</u>

ሸ. የዞን መስተዳድር ሊቀመንበር ..... ስብሳቢ

ቀ. የዞን›› ኢ/ማ/ዘርፍ ኃላፊ ....አባል

በ. ›› ግብርና መምሪያ ኃላፊ ..... ፀሐፊ አባል

ተ. ›› ፕ/ኢ/ል/ መምሪያ ኃላፊ .....››

ኘ. ›› የፋይናስ መምሪያ ኃላፊ .....››

ኸ. ›› የኢ/ን/ቱ/ት/መ/መምሪያ .....››

፲፯ <u>የዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር፣</u>

፩. የኢንቨስትመንት አዋጅ በሚደነገገው መሠረት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችና ተግባራዊነታቸው በቅርብ ይቆጣጠራል ለባለሃብቶች አስፈላጊው ድጋፍ ይሰጣል።

፪. የሁሉም ወረዳዎች የኢንቨስትመንት ሪፖረት ያጠናቅራል ለጽ/ቤቱ ያቀርባል።

፫. በቦርድና በክልሉ ኢንቨስትምንት ጽ/ቤት የተላለፉትን የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል።

፬. ኢንቨስትመንት ለማጠናከር ተፈላጊ ባለሙያዎችን በህጉ መሠረት እንዲቀጠሩ ያደርጋል።

፲፰. <u>የወረዳ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ አባላት፡-</u>

፩. የወረዳ ም/ቤት ሊቀመንበር ..... ሰብሳቢ

፪. >> ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ .....አባል

፫. >> ፋይናንስ ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል

፬. >> ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ >>

፲፱. <u>የወረዳ ኢንቨስትምንት ኮሚቴ ሥልጣንና ኃላፊ</u>

፩.በኢንቨስትመንት በተደነገገው መሠረት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ተግባራዊነት ይቆጣጠራል። ለኢንቨስትመንት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

፪.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ክፍሎችንና ለልማት የሚውሉ አካባቢዎችን ይከልላል፤ጥናት ያካሂዳል የተከለሉ ስፍራዎችን በስፋትና በመጠን ለይቶ ለዞን ኮሚቴ ያቀርባል፤

፫.ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ የወረዳውን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል፤

፬.የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን በተመለከተ አስተማማኝ መረጃዎችን ለዞን ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ያቀርባል።

፭.ከሚመለከታቸው አካል ስለኢንቨስትመንት የሚሰጡትን መመሪያዎችና ውሳኔዎች ያስፈጽማል።

፮. የሚጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

፳. <u>የኮሚቴ ስብሰባዎች</u>

፩.የዞንና የወረዳ ኢንቨስተመን ኮሚቴ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል።

፪.አብዛሃኛው የኮሚቴ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ተቀጥሮ ስብሰባውን ማካሄድ ይቻላል፣፤

፫.የማንኛውም ስብሰባ ላይ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ መሰረት ይሆናል። ድምጽ እኩል ለእኩል ከሆነ የሊቀመንበሩ ወገን አብላጫ ድምጽ ይኖረዋል።

፬.ኮሚቴው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ላይ አማካሪዎች እንዲገኙ ሊያደርግ ይችላል፣

፰. <u>ለኢንቨስትመንት ፈቃድ ማመልከቻ፡-</u>

ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶና ከሚከተሉት መረጃዎች ጋር ተያይዞ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት መቅረብ አለበት።

፩.ስለ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መግለጫ፤

፪.ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የሚፈለጉትን መሳሪያዎችና ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት የሚያስይዝ ዝርዝር

፫.የንግድ ማህበር ሲሆን የማህበሩን መመስረቻ ጹሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣

፬.ማቋቋም ማስፋፋት ወይም መሻሻል ሲሆን የዚሁ አጭር መግለጫ የአፈፃጸም ፕሮግራም ፤

፭.የውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች ሲኖሩ ለተተኪ ኢትዮጵያዊያን ስለሚሰጠው የስልጠና ፕሮግራምና ስለሚተኩበት የጊዜ ገደብ መግለጫ፤

፮.ማመልከቻው በወኪሉ የቀረበ ሲሆን የውክልና ስልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ፤

፯.እንደ ፕሮጀክቱ ልዩ ፀባይ አግባብ ያላቸው ሌሎች መረጃዎች፤

<u>፰፩. ስለኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ፡-</u>

፩.በስራ ላይ ያሉት የፌደራሉና የክልሉ ህግ የማይጥስ መሆኑን በተለይም የአካባቢ ጥበቃን የሚመለከት በወጡ ህጎች የተደነገጉ ሁኔታዎችን የሚያሟላ መሆኑን በአስር ቀናት ውስጥ አረጋግጦ ለአመልካቹ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጠዋል።

፪. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

ሀ/ የባለሀብቱን ስምና ዜግነት፤

ለ/ የኢንቨስትመንቱ የስራ መስክ፤

ሐ/ ኢንቨስትመንቱ የሚካሄድበትን የአካባቢ ወይም አስተዳደር፤

መ/ የኢንቨስትመንቱን ካፒታል መጠንና፤

ሠ/ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ያስፈልጋሉ ብሎ ያመነባቸውን ሌሎች ዝርዝሮች።

፫.የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው ባለሃብት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክትን ግንባታ አጠናቆ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ የንግድ ወይም የስራ ፈቃድ እንዲያወጣ አይጠይቅም፤

፬.አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ሳይፈቅድ የኢንቨስትመንትን ፈቃድ ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ አይቻልም።

፭.የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሌላ ሰው ሲተላለፍ ወይም በይዘቱ ላይ ሌሎች ለውጦች ሲያጋጥሙ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት አካል ቀርቦ መሻሻል አለበት

<u>፰፪. የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት</u>

፱. ለኢንቨስትመንት ፈቃድ ምርት ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት እሰከ ሚጀምርበት ሆኖም ባለሀብቱ ስለኢንቨስትመንቱ አፈፃፀም ሂደት በየስድስት ወሩ አግባብ ላለው ኢንቨስትምንት አካል ሪፖርት ማቅረብ አለበት፣

፲. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ የአንድ ዓመት ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት፣

፲፩. አግባብ ያለው ኢንቨስትመንት አካል ባለሃብቱ የፕሮጀክት ግንባታውም ሊጀመር ወይም ሊጨረስ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ሲያምንበት ፈቃዱን ያድስለታል።

፲፪. <u>የኢንቨስትመንት ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ፦</u>

፩. ባለሃብቱ የኢ/ፌ/ዴ/ሪ ኢንቨስትመንት አዋጅ 37/1988 ወይም የክልሉን ኢንቨስትመንት አዋጅና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እስኪወስድ ድረስ አግባብ ያለው ኢንቨስትመንት አካል የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊያግድበት ይችላል።

፪. አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት አካል ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ በተጨባጭ

ሲረጋገጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል፣

ሀ) ባለሃብቱ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ያገኘው በማታለል ወይም በሀሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፤

ለ) ባለሀብቱ ከህግ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ፤

ሐ) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ፤

መ) የተሠጠው ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው ዓላማ ውጭ ውለው ወይም ከህግ ውጭ ለሌላ ሰው ተላልፈው ከተገኙ ይሆናል።

፫. በሚመለከተው አካል የፈቃድ እገደዳ ወይም ስረዛ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ምክንያቱ ለባለሀብቱ በፅሀፍ መግለጽ አለበት ባለሃብቱም አስተያየቱን እንዲያቀርብ የአንድ ወር ጊዜ ይሰጠዋል።

፬. ባለሀብቱ አስተያየት ካልሰጠ ወይም የሠጠው አስተያየት በሚመለከተው አካል ታይቶ አጥጋቢ ካልሐነ ፈቃድ የማገድ ወይም የመሰረዝ እርምጃ ይወስዳል።

፭. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘበት ባለሀብት ፈቃዱ ከተዘረዘበት ቀን ጀምሮ ሲያገኝ የነበረው ጥቅም ይቋረጥበታል፣

፮.የኢንቨስትምንት ፈቃድን ከሰጠው የክልሉ ኢንቨስትምንት ጽ/ቤት በስተቀር በሌላ በማንኛውም አካል ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ አይችልም።

፯.ፈቃድ የጠፋበት የተበላሸበትና ፈቃድ ለማስተላለፍ ፈቃደዱ ለተመዘገበበት ጽ/ቤት በሚመከተው ምትክ ወይም አዲስ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል

ሆኖም ፤

ሀ) የጋዜጣ ማስታወቂያ በአመልካቹ ወጪ መውጣት አለበት፤

ለ) በ፩ ወር ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ የደንቡን ክፍያ ከተከፈለ በኃላ ምትክ ፈቃድ ይሰጠዋል፤

ሐ) የተበላሸ ፈቃድ ለጽ/ቤቱ ሊመለስ ይገባል፤

መ) ፈቃድ ሲተላለፍ የቀድሞው ለጽ/ቤቱ ተመላሽ ይደረጋል አዲሱ በስሙ ፈቃድ ይሰጠዋል።

፭፻. <u>ስለ አቤቱታ አቀራረብ፤</u>

በኢንቨስትምንት ፈቃድ በማበረታቻ ጥያቄ ላይ አግባብ ያለው የኢንቨስትምንት አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ባለሃብት ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደአግባቡ ለክልል መስተዳድር አካል ወይም ለለፌደራሉ መንግስት ኢንቨስትመንት ቦርድ ማቅረብ ይችላል።

፭፻. <u>ስለኢንቨስትመንት ዋስትናና ጥበቃ</u>

ለኢንቨስትመንት የዋለ ሀብት ለህዝብ ጥቅም ሲባልና በህግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊወሰድ ወይም ሊወረስ አይችልም።

፪. ለኢንቨስትመንት የዋለ ሀብት ለህዝብ ጥቅም ሲባልና በህግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊወሰድ ወይም ሊወረስ አይችል።

፫. ለኢንቨስትመንት የዋለ ሀብት ለህዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ ወይም ሲወረስ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ ሳይዘገይ መክፈል አለበት።

፭፻. <u>ስለካፒታል ገደቦች</u>

በግል ባለሀብቶች ስለሚካሄዱ የሥራ መስኮች በመንግስት ስለሚካሄዱ የስራመስኮችና ስለቴክኖሎጂ ሽግግር ውሎች በሚመለከት በኢት/ፌደ/ዲሞ/ሪፐ/ ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፱፷፯ ላይ የተደነገጉ በተመሳሳይ በዚህ አዋጅ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፭፻. <u>ስለማበረታቻዎች፤</u>

በአዋጅ ቁጥር ፱፹፯/፹፬ ዓ.ም የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጽ/ቤቱ የክልልን ኢንቨስትምንት ማበረታቻዎች በደንቡና መመሪያ ለባለሀብቶች ያቀርባል።

፭፻. <u>ውሃ ስለማግኘትና ስለአጠቃቀሙ፤</u>

፪.ማናቸውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ውሃ ከሚመለከተው የክልል መንግስት አካል ጋር በሚያደርገው ውል መሰረት ለማግኘት ይችላል።

፫. ስለ አጎራባች ውሃዎች አጠቃቀም በሚመለከት የኢት/ፌደ/ዲሞ/ሪፐ መንግስት የውሃ ሃብት ልማት ሚ/ር በወጣው ህግና ደንብ መሰረት ባለሃብቱ በኢቨስትምንት ውሃ ሊያገኝና ሊጠቀም ይችላል።

፭፻. <u>ስለማዕድን አጠቃቀም፤</u>

ባለሀብቱ ለኢንቨስትመንቱ ስለሚጠቀምባቸው ማዕድናት የክልሉ ስራና ከተማ ልማት ማዕድንና ኢንጂነር ቢሮ በሚያዋጣው ደንብና መመሪያ መሠረት ሊጠቀሙ ሲችል በማዕድን ክፍል ኢኮኖሚ ኢንቨስትምንት ስለሚደረግበት ሁኔታና ማበረታቻ አፈቃቀድ የኢ.ተ/ፌዴ/ዲሞ/ሪፐ/ መንግስት የማዕድንና ኢነርጂ ሚ/ር ህግ መሰረት ይወሰናል።

፴.<u>የኢንቨስትመንት መረጃዎችን ስለማስተላለፍ እና ይህንን አዋጅ ስለመተግበር ግዴታ፤</u>

ማናቸውም የክልል መንግስት አካል ስለክልሉ ሀብት ክምችት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መረጃዎችን የማስተላለፍና ግዴታና ይህንን አዋጅ የመተግበር ግዴታ አለበት።

፴፤. በዚህ አዋጅ ስላልተገለፁ የኢንቨስትመንት ጉዳዮች የኢ.ተ/ፌዴ/ዲሞ/ሪፐ መንግስት ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ላይ የተደነገጉበት በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፴፯. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፡</u>

፤. ይህ ዋጅ በወጣበት የበጀት ዓመት በህግ መሰረት የተሰጠ ወይም የታደሰ ፈቃድ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጠ ወይም እንደታደሰ ይቆጠራል።

፯.ማንኛውም ፈቃድ ይህ አዋጅ በወጣበት ዕለት ፈቃድ በተሰጠበገት ህግ መሰረት ሊታደስ የሚችል ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ይታደሳል፡

፴፴. <u>ቅጣት፤</u>

አግባብ ባለው ሌላ ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፤

፤. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሳይኖረው የሚሰራ ማናቸውም ሰው ያለፈቃድ በሰራበት ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚወሰነውን ገቢ እጥብ የገንዘብ መቀጫና ከ፫ እስከ፯ ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

፯. ማንውም ሰው ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ የኢንቨስትመንት ስራውን የስራፈቃዱን ያወጣ ወይም ያሳደሰ እንደሆነ በሀሰት መረጃ መስራቱ እስከታወቀበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚወሰነውን ገቢ እጥፍ የገንዘብ መቀጫና ከ፯ እስከ፲ ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

፴. ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም የህዝብ ማስታዎቂያዎችን ተላልፎ የተገኘ እንደደሆነ ከብር 3000 እስከ 5000 (ከብር ሶስት ሺ እስከ አምስት ሺ) በሚደርስ መቀጫ እና ከ 6 ወር 1 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

፴. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከምዝገባና ከፈቃድ መስጠት ጋር በተያያዙ የስራ መስኮች ተመድቦ የሚሠራ የመንግስት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ መደለያ በመቀበል ወይም በወዳጅነት ወይም በዝምድና ወይም አግባብ ባልሆነ ሌላ ግንኙነት በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ የምዝገባ ስራ የፈፀመ ወይም እንዲፈፀም ያደረገ ፈቃድ የሰጠ ወይም እንዲሰጥ ያደረገ ፈቃድ ያደሰ ወይም እንዲታደስ ያደረገ ከ 10 ዓመት አስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፤ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(ፒ) የተመለከተው ባለጉዳይ ላይም ተፈፃሚ ይሆናል።

፱. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፵) በተጠቀሰው ወሰወጀል ተሳታፊ በሆኑት ወገኖች ማለትም ከመደለያ ሰጪው ወይም ተቀባዩ ሁኔታውን በቅድሚያ ያጋለጠው ወገን ከወንጀልና ከቅጣቱ ነፃ ይሆናል።

፵፮. ማናቸውም ህጎች ድንጋጌዎች ልማዳዊ አሰራሮች ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፵፯. አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከ ---------- ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል

አይሰኢታ፥----------

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር